# 1. እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቨምበር 30/2020 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፉት የበጋ ሁለት ወራት (ከኦክቶበር እስከ ኖቨምበር) 2020 አብዛኛዉን ጊዜ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ ቢሆንም፤ የኦክቶበር መጀመሪያዉ እና ሁለተኛዉ አስር ቀናት እንዲሁም በኖቨምበር የሶስተኛዉ አስር ቀናት የሴሜናዊ ህንድ ዉቂያኖስ የዉሃ አካል መሞቅ ጋር ተያይዞ በተለያዩ ጊዜያት በተፈጠረዉ የባህር ላይ ሞገድ(Storm) ምክንያት ዕርጥበታማዉ አየር ወደ ሀገራችን እንዲገባና የደመና ሽፋን እንዲፈጠር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በተለይም በምዕራብ አጋማሽና ደቡብ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረዉ ደመና ጠንካራ እና አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ የማስከተል አቅም ነበረዉ፡፡ በመሆኑም በምዕራብ አማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ አንዳንዶቹን ለመጥቀስም ያህል በአቦቦ 114.0ና 57.0፣ በጊኒር 72.0፣ በቻግኒ 47.0ና 45.0፣ በሲርበአባያ 54.0፣ በአርጆ 48.6፣ በነቀምቴ 52.2፣ በደሎመና 43.5፣ በቡሌሆራ 43.5፣ በአዶላ 35.5፣ በአርባምንጭ 33.5ና 42.8፣ ወላይታ ሶዶ 57.9 እና በማጂ 66.0፣ 50.0ና 35.0፣ በሚሜ ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ በተቀሩት ጊዜያቶች ደረቅ ፀሃያማና ነፋሻማዉ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመስተዋሉ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት መጠንም በአንዳንድ የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በደብረ-ብርሃን -3.2፣ -0.5፣ -2.0፣ -1.4፣ -1.2ና -0.8፣ በባቲ -1.5፣ -2.5፣ 0.8፣ 0.5ና 0.4፣ በወገልጤና -1.0፣ 2.2፣ በአምባ ማሪያም 2.8ና 1.4፣ 0.2፣ በአርሲ ሮቤ 4.0ና 3.0፣ በሀረማያ 3.8ና 2.2 እና በመሃልሜዳ 1.0 በዲሴ ይገኙበታል፡፡

ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ (ከኦክቶበር እስከ ኖቨምበር) 2020 የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ በአገዉ አዊ፣ በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በቄለም፣ በምዕራብ፣ በምስራቅና ሆሮጉዱሩ በወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በአርሲና ባሌ፣ በጉጂና ቦረና፣ በሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሊበን በአፍዴር፣ በሸበሌ፣ በኖጎብና በቆራሄ ጀረር ዞኖች ላይ ከ50-400 ሚሜ የሚደርስ ከ10-44 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በትግራይ ክልል ዞኖች፣ በዋግህምራ፣ በኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሁሉም


የሸዋ ዞኖች፣ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች እና በፋፈን ዞን ላይ ከ10-50 ሚሜ የሚደርስ ከ8 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ (ኦክቶበር እስከ ኖቨምበር) 2020 የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችና ሲዳማ ክልል ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ በቄለም፣ በሆሮጉዱሩ፣ በምዕራብና ምስራቅ ወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባቦር፣ በምዕራብ አርሲ፣ በጉጂና ቦረና፣ በሊበን፣ በአፍዴር፣ በሸበሌ፣ በዶሎ፣ በቆራሂ ጀረር፣ በጥቂት ኖጎብና ደገሃቡር ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፣ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡

በአጠቃላይ የበጋው ወቅት አጋማሽ ማለትም በኦክቶበርና በኖቬምበር ወራት የዘነበው የዝናብ መጠን በምዕራብና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ እንደነበረና በመጠን ረገድም ከ10-400 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ እንደተመዘገበ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሁለቱ ወራት ከሚጠበቀዉ መደበኛው የዝናብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በቤንሻንጉል ጉሙዝና አጎራባች በሆኑት የምዕራብ አማራ ኪስ ቦታዎች፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላና በሱማሌ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ ተስተው□ል፡፡ በአጠቃላይ በጋ ወቅት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብና የደቡብምስራቅ አካባቢዎች በአመዛኙ መደበኛ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1ሀ እና 1ለ)። በሌላ በኩል በተለይም በሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ መምጣቱ ተስተዉሏል፡፡




ካርታ 1ሀ እ. ኤ. አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2020 የነበረው ዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 1ለ ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2020 የነበረው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር

## 2. **<u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2020 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>**

በመደበኛ ሁኔታ የበጋ ወቅት አጋማሽ ወራት በአመዛኙ ደረቃማ ሁኔታ የሚያመዝንባቸው ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ያልተጠበቀ ዝናብ የሚታይበትም ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም በዚሁ የበጋ የመጀመሪያዎቹ ወራት የሀገሪቱ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ቆላማ ቦታዎች ወቅታዊ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ ከግብርና እንቅስቃሴ አንፃርም የመኸር አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የሰብል ስብሰባና ድኅረ ሰብል ስብሰባ የሚካሄድበት ሲሆን፤ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ደግሞ የአርብቶ አደሩና ከፊል አረብቶ አደሩ አከባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ እንዲሁም መጠነኛ የሆነ እርሻ እንቅስቃሴ የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው። በተጨማሪም በነዚሁ አካባቢዎች ለከብቶች ግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ የሚሆን እርጥበት የሚያገኙበትና ውሃን በተለያየ ዘዴ ለማከማቸት እድል የሚያገኙበት ወቅት ነው። በአንፃሩ የበጋ ወቅት በአጠቃላይ ሲታይ ለበሽታና ለተባይ መከሰትና መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ሊኖር የሚችልበት ከመሆኑ አንጻር የሰብሎችን ጤናማ ሁኔታ በቅርበት ክትትል ማድረግ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው፡፡ በበጋ ወቅት የሙቀት መጠን ከአዝርዕት ጤናማ እድገት አኳያ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ሲሆን፤ በአንዳንድ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በደቡብ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ውርጭ የሚከሰትበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለይም በአበባና ፍሬ በመያዝ ላይ ለሚገኙም ሆነ ለፍራፍሬ ተክሎች ከፍተኛ ቅድመ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚያስፈልግበት ወቅት ነው፡፡

እ.ኤ.አ ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር 2020 በተለይም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው። ነገር ግን ከወሩ አጋማሽ በኋላ በአብዛኛዎቹ አካባቢውች ላይ የእርጥበት ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንደመጣ የግብርና ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን በተለይም በመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ወደ ሀገራችን ይገባ የነበረው ዕርጥበት እየቀነሰ በመምጣቱ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ ሁኔታ አመዝኖ ነበር። ሆኖም የእርጥበት ሁኔታው ይበልጥ ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ የነበረው ሲሆን ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከረ ከመጣው ደረቅ የአየር ጠባይ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በደጋማው የሀገሪቱ አካባቢዎቸ ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ በመምጣቱ አንዳንድ አካባቢዎቸ ከአምሰት ድግሪ ሴልሽዬስ በታች የሆነ ዝቅተኛ ሙቀት ተመዝግቧል።


በተለይም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ የታየው እርጥበታማ ሁኔታ በወቅቱ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችና ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ለማሟላት አዎንታዊ ሚና የነበረዉ ሲሆን በሌላም በኩል ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ሚናው ከፍተኛ ነበር። በአንጻሩ በአንዳንድ አካባቢዎቸ ላይ የታየው ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ለደረሱና በመሰብሰብም ሆነ በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ መልኩ በተለለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱና ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው የመኸር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች በመጠኑ አሉታዊ ጎን ነበረው። ከቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት ጋር ተያይዞ በደጋማ አካባቢዎቸ ላይ የታየው የሌሊትና የማለዳ ቅዝቃዜ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በጥቂቱ አሉታዊ ተጽእኖ ነበረው፡፡

ባሳለፍነው የኖቬምበር ወር 2020 በተለይም በሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማዉ እርጥበት ከፀሃያማነትና ከነፋሻማነት ጋር እንዲሁም ከማለዳና ከሌሊቱ ቅዝቃዜ ጋር ተዳምሮ በአመዛኙ ተስተዉሏል፡፡ከሚጠበቀዉ ወቅታዊ የግብርና እንቅስቃሴ አንጻር ሰብል ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ይሁን እንጂ በመጀመሪያዉና ከሶስተኛዉ አስር ቀናት አጋማሽ ጀምሮ የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም የበጋ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የእርጥበታማ ሁኔታው በአመዛኙ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት በደጋማው አካባቢ ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋጽዕ ነበረው። በሌላ በኩል ከደረቃማዉ የአየር ሁኔታና ከደመና ሽፋን መሳሳት ጋር ተዳምሮ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ባልደረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት በኦክቶበር እና በኖቨምበር የነበራቸው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በተለይም የክረምቱ ሲስተም ቀስ በቀስ ከመዳከሙ ጋር ተያይዞ የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት እየቀነሰ በአንጻሩ በምእራብ አጋማሽ እና በመካከለኛዉ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በተወሰነ ደረጃ የቆየበትና በሂደትም የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ወደ ሆኑት ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ እንደነበረ ተስተውሏል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ሁኔታ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙ ለደረሱና ተጨማሪ እርጥበት ለማያስፈልጋቸው ሰብሎች በጎ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ መልኩ በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እርጥበቱ የተሻለ ገፅታ የነበረው መሆኑ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ይገኙ ለነበሩ ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚገኙ ቋሚ ተክሎች በጎ ሚና ነበረው ((ካርታ 2ሀ እና 2ለ)፡፡ ፡፡

ካርታ 2ሀ፡ የኦክቶበር ወር 2020 የእርጥበት ሁኔታ


ካርታ 2ለ፡ የኖቬምበር ወር 2020 የእርጥበት ሁኔታ




## 3. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1- እስከ ኖቬምበር 30 /2020 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ኦክቶበር እና ኖቬምበር 2020 የበጋ ወራት በአብዛኛዎቹ የበጋ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል፡፡ በኦክቶበር ወር የተሻለ የእርጥበት መጠን እና ስርጭት የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛዉ ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ የታችኛው አባይና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ተስተውሎባቸው ቆይተዋል፡፡ በኖቬምበር ወር የእርጥበት ስርጭቱ ከኦክቶበር ወር በተሻለ ሁኔታ የተስፋፋ ሲሆን፤ በስርጭት ግን የቀነሰ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛዉ ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ በጥቂት

የተከዜ እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ኪስ ቦታዎች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የነበራቸው ሲሆን፤ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን እና የሰሜን ምስራቅ አጋማሽ የሚገኙ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ነበር (ካርታ 5ሀ እና ለ)፡፡




ካርታ 3ሀ፡ በኦክቶበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ካርታ 3ለ፡ በኖቬምበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን


## 4. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1- እስከ ኖቬምበር 30 /2020 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ የነበረው ተፅዕኖ ግምገማ


ለወባ መፈጠር ምቹ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች (ዝናብ፣ ምዝን የአየር ርጥበትና አማካይ የሙቀት መጠን) በመጠቀም የወሩ የዝናብ መጠን 80 ሚ.ሜ. እና ከዛ በላይ፣ አማካይ የወሩ ምዝን የአየር ርጥበት 60% እና በላይ እንዲሁም አማካይ የወሩ የሙቀት መጠን በ18 °c እና 32 °c መካከል ሲሆኑ፤ እነዚህን መስፈርቶች በመጠቀም ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ ጠቋሚ መረጃ ይዘጋጃል፡፡

በሌላ በኩል የአየሩ ሁኔታ ለሰው ልጅ በአንድ አካባቢ ለመኖር ምቹ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን (አማካይ የሙቀት መጠን፣ ምዝን የአየር ርጥበትን በመጠቀም የሚገኘው የአየር ሁኔታ ኢንዴክስ መረጃ ይዘጋጃል፡፡ በዚሁ መሠረት የጥቅምትና የህዳር ወራት ግምገማን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የዝናብ፣ የሙቀትና የአየር ርጥበትን ስንመለከት ጥቂት የሀገሪቱ ክፍሎች የዝናቡ መጠን ከ80 ሚ.ሜ. በላይ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ በተጨማሪም የሙቀት ሁኔታ ከጥቂት የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ በ18 oc እና 32 oc መካከል ሆኖ ሰንብቷል፡፡ እንዲሁም ምዝን የአየር እርጥበቱ በጥቂት የሀገሪቱ

ክፍሎች ከ60% በላይ እንደነበር የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ በዚሁ መሠረት ለወባ መፈጠር በጥቅምት ወር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች፡-አብዛኛው ቤኒሻንጉልጉምዝ፡ ምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፡ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፡ጋምቤላ፡ ጥቂት ሰሜን ምዕራብ አማራ እና ደቡብ ምዕራብ የሶማሌ ክልሎች ምቹ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በህዳር ወር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፡ ጥቂት የደቡብ ጋምቤላ እንዲሁም የደቡብ ኦሮሚያ ኪስ ቦታዎች ላይ ምቹ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለወባ መፈጠር አመች የአየር ሁኔታ እንዳልነበረባቸው መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 4ሀ ና 4ለ)፡፡




ካርታ 4ሀ፡-የጥቅምት ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች

ካርታ 4ለ፡-የህዳር ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች

**<u>መግለጫ፡-</u> በቢጫ ባግራዉንድ ቀይ መስመር ካሬ ያለባቸው ቦታዎች ለወባ መፈጠር አመቺ የአየር ሁኔታ ያለባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡**

በአጠቃላይ የ2020 የበጋ ወቅት አጋማሽ የወባ ትንኝ ለመራባት ምቹ የአየር ሁኔታን ስንመለከት ከጥቅምት ወር ይልቅ በህዳር ወር በአብዛኛው የበጋ ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ከወር ወደ ወር እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ለሰው ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታን (THI Value) ስንመለከት በሁለቱም ወር ላይ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ምቹ የአየር ሁኔታ (Comfortable) እና አብዛኛው የመካከለኛ ምቾት (Moderate) የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 5. ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2020 እስከ ጃንዋሪ 31/ 2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ወራት በአብዛኛው የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ገፅታዎች የሆኑት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝኑበት ከመሆኑም ሌላ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሚያይልበት ጊዜ ነው። በአንፃሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ አማራ ቦታዎች በሆኑት የሰሜንና የደቡብ ወሎ አካባቢዎች ላይ ዝናብ ይዘንባል። በተጨማሪም ከመደበኛ ሁኔታ ወጣ ባለ መልኩ በአንዳንድ ዓመታት ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ይከሰታል።

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ አብዛኛው ክፍል የባህር ወለል ሙቀት እየቀነሰ እንደሚገኝ የሚስተዋል ቢሆንም፤ በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት ኢ.ኤ.አ 2020-21 (ዲሴምበር እና ጃንዋሪ) የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው በታች (La-Nina) የመሆን እድሉ እስከ 95% ሊደርስ እንደሚችልና እንዲሁም የህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (Neutral IOD) ሆኖ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

<u>በአጠቃላይ አሁን ከሚስተዋለውና ለመጪዎቹ ሁለት ወራት ከተተነበዩ የባህር ወለል ሙቀትና የከባቢ አየር ሁኔታዎች በመነሳት በአብዛኛው የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ስለሚያመዝን የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል። በተጨማሪም የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ፣ በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምስራቅ ክፍሎች ከመደበኛ በታች ዝናብ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህም ሌላ የበጋው ወቅት ማብቂያ አካባቢ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በምሥራቅ አማራ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።</u>

## 6. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2020 እስከ ጃንዋሪ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት ማለትም ከዲሴምበር እስከ ጃንዋሪ 2020/21 በተሰጠው የአየር ትንበያ መሰረት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ይህ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ለድኅረ ሰብል ስብሰባ አዎንታዊ ጎን እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ የሚኖረው የእርጥበት እጥረት በአካባቢዎቹ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላትም ሆነ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይጠበቃል፡፡ ከሚጠበቀው ቅዝቃዜ ጋር በተያያዘ በተለይም በቋሚ ተክሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ከደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል የተተነተኑ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም በመስኖ የሚለሙ ሰብሎች፣ አትክልቶችና የፍራፍሬ ተክሎች ሊጎዱ ስለሚችሉ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስለሚጠበቅ በነዚህ አካባቢዎች ላይ ለግብርናዉ እንቅስቃሴ አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ እና የሚመለከታቸዉ አካላት አልፎ አልፎ የሚገኘዉን ዉሃ በማቆር እንዲሁም የተለያዩ ዘደዎችን መተግበር በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በአንዳንድ በልግ ተጠቃሚ በተለይም በደቡብ፣ በመካከለኛዉና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች በጃንዋሪ ወር አካባቢ የሚጠበቀዉ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ለሚቀጥለው በልግ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴና የማሣ ዝግጅት እንዲሁም በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አሉታዊ ተፅኖ ይኖረዋል፡፡

## 7. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2020 እስከ ጃንዋሪ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት (በዲሰምበር እና በጃንዋሪ) በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ  አመዝኖ የሚቆይ ሲሆን፤ በደቡብ፣ ሰሜን ምሥራቅ እንዲሁም መካከለኛ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በዚህም መሰረት ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ

እርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል (ዲሰምበር እና ጃንዋሪ) በበጋው ወራት የሚኖረውን የሙቀት መጨመር በበጋ ወራት ውስጥ የሚስተዋል ክስተት በመሆኑ በተፋሰሶች ላይ የእርጥበት እና በግድቦች ላይ የውሃ መቀነስ እንዲሁም ከፍተኛ ሙቀትና የተራዘመ ደረቅ ሰሞናት መኖሩ በትነት ምክንያት የውሃ ብክነትን ሊያባብስ የሚችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ እጥረት በሚታይባቸው ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው እርጥበት በመጠኑም ቢሆን ለውሃ ሀብት ግብዓት የሚያግዝ በመሆኑ ጥሩ አሰተዋፆ ይኖረዋል፡፡ የተቀሩት አብዛኛቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የእርጥበት መጠን ስር ሊቆዩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

## 8. <u>እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2020 እስከ ጃንዋሪ 31/2021 የአየር ሁኔታ ትንበያና ምክሮች በጤናው ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት (በዲሰምበር እና በጃንዋሪ) በግምገማው ላይ እንደተገለፀው ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ሆኖ በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው ለወባ በሽታ መስፋፋት ተጋላጭ የነበሩ ቦታዎችን መጠቆምና ከውሃ ጋር ተያይዞ ሊመጡ የሚችሉ ውሀ ወለድ በሽታዎች ሊኖሩ መቻላቸውን መጠቆም ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የምንጠቀምባቸው ክራይቴሪያዎች የዝናብ፣ የሙቀትና ምዝን የአየር እርጥበትን እንዲሁም በመ/ቤቱ ትንቢያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠውን የዝናብ ትንበያ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚጠበቁት አካባቢዎች በጥቂት የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ዝቅተኛና መካከለኛ ቦታ ያላቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለወባ መፈጠርና መስፋፋት አመቺ የአየር ሁኔታ በመጠኑ እንደሚኖራቸው ያሳያል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ደረቅና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ስለሚያመዝንባቸው በመጭዎቹ ሁለት ወራት ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ አይኖራቸዉም፡፡

**በመጨረሻም ሁሉም የሚመለከተው አካላት በየወሩ፣ በወቅቶች አጋማሽና በየወቅቱ የሚሰራጩትን የብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ መረጃወችን በመከታተልና ጥቅም ላይ በማዋል አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ እንዲደርጉ እንመክራለን፡፡**